# የማይቀር አይቀርም!

(ከመብረቁ ዘቋራ)

ታጋይ እየሞተ፣ ታጋይ ቢታሠርም፣
መተካት አይቀርም፣ የማይቀር አይቀርም!

የአረቡን አመፅ፣ ፀንሦ የወለደው፣
የተጠራቀመው፣ የህዝብ ብሶት ነው።
በኢትዮጵያም፣ ይህ ፈፅሞ አይቀርም!
አንዱ ዓለም፣ እስክንድር፣ እንዲሁም ሌሎቹ፣ ተጠያቂ አይሆኑም።

በራሱ ጥላ ሞት፣ የሚባንን መንግሥት፣
ሺህ አዋጅ ቢያወጣ፣ ህዝብን ለማስቦካት፣
ታጋዮችን ቢያስር፣ ቢያበዛ ፍርድ ቤት፣
የማይቀር አይቀርም፣ ቀን የደረሰ ዕለት።

ደንጋጣው ወያኔ፣ ቢጠላም ቢወድም፣
የጊዜ ጉዳይ ነው፣ መገርሰሱ አይቀርም!

ለሆዳሙ ዳኛ፣ ግፍ ለማይሠማው፣
የዕድሜ ልክ እስራት፣ መበየን ቀላል ነው፤
ግን "እግረ ቀጭን ይሞታል ሲባል፣ እግረ ወፍራም ይሞታል" ይባላል፣
ይብላኝ ያ ቀን ሲደርስ፣ ለነፍርደ-ገምድል፣
በሰፈሩት ቁና፣ ዕዳቸው ሲከፈል።

ሽብር ህግ ሆኖ፣ ከወጣ ጀምሮ፣
ስንት ንፁህ ዜጋ፣ ታፈሰ በጓሮ?!
ጥላቸውን ማመን፣ ያቃታቸው ሁሉ፣
ህዝብን አሸባሪ፣ አድርገው ያያሉ፣
እንዲህ ተሸማቀው፣ እንዴት ይኖራሉ?!
የሀሰት ምስክር፣ ፈጥረው ይቆጥራሉ!
ህሊና የላቸው፣ ከምን ይማራሉ?!

የነመለስ ምላስ፣ በሀሰት ተስሎ፣
ጭፍሮቹን አብዝቶ፣ እሱን አስመስሎ፣
ወናፍ ብቻ ሆኗል፣ አቅማዳ ቀልቀሎ፣
ህዝቡን ሳይጨርሰው፣ እንደዚህ አቁስሎ፣
በውነት ያስፈልጋል፣ መራር ተጋድሎ።

"አየ ጉድ! አየ ጉድ!” እስከመቼ ድረስ?!
“ጅቡ ከሚበላን፣ በልተን እንቀደስ!”
ሠላማዊ ትግል፣ ፍፁም ለማይገባው፣
ከአመጽ በስተቀር፣ ምን አማራጭ አለው?!
አንዱ ዓለምን ያህል፣
እስክንድርን ያህል፣ ለዕድሜ ልክ ስናጣ፣
አንድ መሆን አቅቶን፣ እንዴት ሙሾ እናውጣ?
በአበበ ትንፋሽ፣ አንገቱን በሚጥል፣ በዚያ በደንጋጣ!
እንደምን ይወሰን፣ ያገራችን ዕጣ?!

(ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ. ም.)